


DISCOVER

ITS BEAUTY

ክፍል 2

## የአደም እና ሐዋ

# ሃይማኖት

ዶ/ር ናጂ ኢብራሂም



**አንድ መልእክት!**

አደም እና ሐዋ ከተፈጠሩበት ጊዜ አንስቶ፣ በታሪክ ዘመናት፣ አንድ እውነተኛ መልእክት ያለው አንድ እውነተኛ ሃይማኖት ብቻ ለሰው ልጆች በተደጋጋሚ ሲደርስ ቆይቷል። ሰዎች በፈጣሪያቸው እንዲያምኑ እና እርሱን ብቻ እንዲያ መልኩ ለማዘዝ፣ ሰዎችን እንዲያስታውሱ እና ወደ ትክክለኛው ጎዳና እንዲመ ለሱ፤ ብዙ ነብያት እና መልእክተኞች - አደም፣ ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ኢሳ እና ሙሀመድ - አንድ አይነት የሆነ ከአላህ የመጣ ሀይማኖትን እንዲከተሉ እና ይህንኑ መልእክት እንዲያስተላልፉ ከእውነተኛው አምላክ ከአላህ ዘንድ ተልከ ዋል።

**እውነተኛ አምላካችሁ፣ አላህ፣ አንድ ነው። እሱንም ብቻ አምልኩት።**

እነዚህ ነቢያትና መልእክተኞች ሁሉ የሰበኩት መልእክት ተመሳሳይ ነው፣ ስለዚህ ሃይማኖታቸው አንድ መሆን አለበት!

ለአላህ (አምላክ) መገዛት ነው የመልእክታቸዉ ዋና ሀሳብ። ይህ **'መገዛት' የሚለው ቃል የዐረብኛው ቃል 'እስልምና'** ትርጉም ነው።

ለአላህ መገዛት ወይም **'እስልምና'** የአደም እና የሁሉም የአላህ ነቢያት እና መልእክተኞች እውነተኛ ሃይማኖት መሆኑን ቁርኣን ያረጋግጥልናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢሳ ተከታዮቹን የአምላክን ፈቃድ እንዲያደርጉና ትእዛዛቱን እንዲጠብቁ እንዳስተማራቸው ብዙ መግለጫዎችን ይጠቅሳል። በተመሳሳይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእስልምና (ለአላህ መገዛት) ትርጉምን ያመላክታል፦

እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ (ያእቆብ 4:7)

**'ሙስሊም'** የሚለው ቃል ፈቃዱን ለእውነተኛው አንዱ አምላክ ያስገዛ ሰው ማለት ነው። ስለዚህ ሙስሊሞች የአደም፣ የኑህ፣ የኢብራሂም፣ የሙሳ፣ የኢሳ፣ የሙሐመድ እና የቀሩት ነብያት እውነተኛ ተከታዮች ናቸው።



እስራኤል ሆይ፥ ስማ፡ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ጌታ ነው። (ዘዳግም 6:4)

እኔ እግዚአብሔር ነኝና ከእኔም በቀር ሌላ የለም; እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔ ያለ ማንም የለም። (ኢሳያስ 46: 9)

ሉዓላዊው ጌታ ሆይ፥ እንዴት ታላቅ ነህ! በጆሮአችን እንደሰማን እንዳንተ ያለ ማንም የለም ካንተ በቀር አምላክ የለም። (2 ሳሙኤል 7:22)

ታውቁኛላችሁ እና ታምኑኛላችሁ እናም እኔ አምላክ እንደሆንኩ ልትረዱ ትችላላችሁ። ከእኔ በፊት አምላክ አልነበረም ከእኔም በኋላ የለም። እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ አዳኝ የለም። (ኢሳይያስ 43:10-11)

አቤቱ፥ አንተን የሚመስልማንም የለም፥ በጆሯችንም እንደ ሰማን ሁሉ ከአንተ በቀር አምላክ የለም። (1 ዜና መዋእል 17:20)

እኔ የፊተኛው፣ የመጨረሻው፣ ብቸኛው አምላክ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም። (ኢሳይያስ 44: 6)

ሌላ አምላክ የለም። “በመላው አለም ያላችሁ ሰዎች፣ አሁን ወደ እኔ ተመለሱ እና ዳኑ! እኔ ብቸኛ አምላክ ነኝ። የገባሁት ቃል እውነት ነው ፣ እናም እሱ አይ ቀየርም እኔ በእኔነቴ ሁሉ ቃል እገባለሁ፤ ሁሉም መጥቶ በፊቴ ይንበረከካል። (ኢሳይያስ 45:21-23)



እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ እንዲህ ብሎ ጠየቀው፣ መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? እርሱም (ኢየሱስ) ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም። (ማቴዎስ 19:16-17)

የዘላለም ሕይወት ማለት እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተን ማወቅ እና የላ ክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ማለት ነው። (ዮሐንስ 17:3)

አምላክህን እግዚአብሔርን አምልክ እርሱንም ብቻ አምልክ! (ማቴዎስ 4:10)

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አንተም ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም፥ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ትእዛዝ የለችም። (የማርቆስ ወንጌል 12:29-31)

ጸሓፊውም። መልካም ነው፥ መምህር ሆይ፤ አንድ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ የለም ብለህ በእውነት ተናገርክ፤ (የማርቆስ ወንጌል 12:32)

አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካ ከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። (1 ጢሞቴዎስ 2:5)

ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት፡- “ትምህርቴ ከላከኝ ቢሆን እንጂ ከራሴ አይ ደለም።” (ዮሐንስ 7:16)



# አንድ እውነተኛ አምላክ በቁርኣን ውስጥ

**አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፣ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው።** (2፡163)

**በል «እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደምᎏ አልተወለደምም፡፡ ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም፡፡»** (112፡1-4)

**ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ።** (21:25)

**አምላካችሁ በእርግጥ አንድ ነው።** (37:4)

**ከአላህ ጋር አምላክ አለን? አላህ (በእርሱ) ከሚያጋሩዋቸው ሁሉ ላቀ።** (27፡63)

**ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ከርሱ በቀር (በእውነት የሚመለክ) አምላክ የለም። ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ ስለዚህ ተገዙት፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው።** (6፡102)

**ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያል ታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።** (9፡31)



የነቢዩ መስጊድ፣ መዲና፣ ሳዑዲ አረቢያ

# ማጠቃለያ

ሁሉም የአላህ ነቢያትና መልእክተኞች አደም፣ ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ሙሰ፣ ኢሳ እና ሙሐመድ-በአንድ አምላክ በሆነው በፈጣሪ አላህ የተላኩት አንድ አይነት መል እክት ለማድረስ ነው።

**እውነተኛው አምላክ አላህ አንድ ብቻ ነው። እሱን በብቸኝነት አምል ኩት።**

እነዚህ ነብያትና መልእክተኞች ሁሉም የሰበኩት መልእክት አንድ በመሆኑ፣ ሃይ ማኖታቸውም አንድ መሆን አለበት! ታዲያ የእነዚህ ነብያትና መልእክተኞች ሃይማኖት ምንድን ነው?

አላህ ፈቃድ መገዛት የመልእክታቸው ዋና ሀሳብ ነው። ይህ **'መገዛት'** የሚለው ቃል የዐረብኛው ቃል **'እስልምና'** ትርጉም ነው።

ቁርአን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ **'እስልምና'** የአደምና የሐዋ እና የዘሮቻቸው እውነተኛ ሃይማኖት መሆኑን ያረጋግጣል።

በመጨረሻ፣ መዳንን ለማግኘት፣ ከላይ የተጠቀሰውን መልእክት በፈቃደኝነት እና በሙሉ ልብ መቀበል እና ማመን አለብን። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም! በተጨማሪም በሁሉም የአላህ እውነተኛ ነቢያት (ነብዩ ሙሐመድን ጨምሮ) ማመን እና እውነተኛ ሃይማኖታቸውን፣ መመሪያቸውን እና አስተምህሮቶቻ ቸውን መከተል አለብን።

**ይህ የደስታ መግቢያ በር ነው፣ የዘላለም ሕይወት!**



# በእስልምና ውስጥ የዋና ስሞች ፍቺዎች

**አላህ፦** በአረብኛ አላህ ትክክለኛው የአንዱ እውነተኛ አምላክ የሆነዉ ፈጣሪ ስም ነው። እስልምና አላህ የሰው ልጆች ሁሉ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ያስ ተምራል።

**ሙሐመድ፦** የአንዱ እውነተኛ አምላክ የመጨረሻው ነቢይ፣ ፈጣሪ የሆነው አላህ፣ ለሰው ልጆች ሁሉ የላከው ነው። ሙሐመድ ሰዎች ሁሉ አላህን (አምላ ክን) በብቸኝነት እንዲያመልኩ አዟል።

**እስልምና፦** ለእውነተኛው አምላክ አላህ ፈቃድ መገዛት።

**ሙስሊም፦** ለአንዱ እውነተኛ አምላክ አላህ ፈቃድ የተገዛ።

**የተከበረው ቁርኣን፦** አንድ እውነተኛ አምላክ የሆነው የአላህ የመጨረሻ ቃል። ለነቢዩ ሙሐመድ የወረደ።


**መስጂድ፦** ሙስሊሞች በዋናነት ለሶላት እና ለአምልኮ የሚጠቀሙበት ንፁህ የስግደት ቦታ ነው።




አላህ በአረብኛ



አላህን (እውነተኛውን አምላክ) የሚማፀን ሙስሊም



የተከበረው ቁርኣን



ሙሐመድ በአረብኛ

# የማወቅ ጉጉት አልዎት?

የማወቅ ጉጉት ካሎት እና ስለ እስልምና ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እባክዎን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፦

**www.discoveritsbeauty.com**

## የውበቱን ያግኙ ተከታታይ ቡክሌቶች፦

1. ከብዙው በትንሹ
2. የአደም እና የሐዋ ሃይማኖት
3. የእስልምና መሠረቶች
4. የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ
5. የእርሱ መልካም ስሞች
6. የመጨረሻው ወህይ
7. የመጨረሻው መልእክተኛ

## ጠቃሚ ኢስላማዊ ድረ-ገጾች፦

**http://www.allahsquran.com**

**http://www.quranexplorer.com**

**http://www.islamhouse.com**

**http://www.edialogue.org**

**http://www.islamreligion.com**

**http://www.newmuslimguide.com**

**http://www.guidetoislam.com/en/**

# የእምነት ምስክርነት (የእስልምና መግቢያ በር)

“ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”

በአረብኛ እንዲህ ይነበባል፦

أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمدا رسول الله

ሲነበብ ይህን ይመስላል፦

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ሏህ**

**ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ**

ይህ አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው። የእስልምናን እውነተኛነት፣ ውበት እና ቀላልነት አንድ ላይ ይዟል።






GLOBAL ACADEMY FOR TRANSLATION AND EDUCATION (GATE)
LONDON | THE UNITED KINGDOM

በAL-ANDALUS GROUP LTD የተተረጎመ
www.alandalusgroup.org

كتاب دين آدم وحواء باللغة الامهرية